# ዓለምለኸ ማሕበር ዴሞክራሲያዊያን ተጋሩ

## አለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር.

**International Tigrean Democratic Association**

itda2005@yahoo.com

ጥር 2001 ዓ.ም

## 1. በሀገር ደረጃ የመደራጀት አስፈላጊነት

ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር (ዓአትዴማ) ከዲሰምበር 2004 ጀምሮ እስካሁን በሲቪክ ማህበርነት ተደራጅቶ የትግራይ ተወላጆችን በማሰባሰብ የህወሓት/ኢህአዴግ ሽብርተኛና ከፋፋይ አገዛዝን በማስወገድ ትክክለኛ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሀገራችን ለመመስረት በሚደረገው ትግል የራሱን አስተዋጽኦ ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። ማህበሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በሀገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ያገዛዙን አሰቃቂ እርምጃዎች በመቃወም በርካታ መግለጫዎችን አውጥቷል፣ በማህበሩ አመራርና በአባላቱ አማካይነት በተለያዩ ስብሰባዎችና፣ ረዲዮ ጣቢያዎች በመቅረብ በልዩ ልዩ ርእሰ ጉዳዮች ገለጻና ቃለ ምልልስ አድርጓል።

ዓአትዴማ በብሄር ደረጃ ቢደራጅም ከጅምሩ ይዞት የተነሳው ዓላማ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት መጠበቅ አስፈላጊነት፣ ዜጎቿ ሁሉ በእኩልነት የሚኖሩባት አንዲት ኢትዮጵያ የመኖር አስፈላጊነት፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ያለምንም ገደብ የመከበር አስፈላጊነት፣ በሀገራችን የህግ የበላይነት መስፈንና ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል የመታየት አስፈላጊነት፣ አሁን ስልጣን ላይ ያለው በመለስ ዜናዊ የሚመራው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ለነዚህ ለገለጽናቸው ዓላማዎቻችን ተግባራዊነት ትለቁ እንቅፋት ስለሆነ ይህ አገዛዝ መወገድ እንዳለበት በግልጽ ያስቀመጡ ነበሩ፣ አሁንም ናቸው።

ዓአትዴማ እነዚህ ዓላማዎች እንደያዘ በ2004 ራሱን ሲያደራጅ በብሄር ደረጃ ለመደራጀት ያስፈለገበት ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች ነበሩ። እነሱም አንደኛ በመለስ ዜናዊ የሚመራው ህወሓት ትግራይን ብቸኛ ግዛቱ በማድረግ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚዎች ከትግራይ ክልል ውጭ ባደረገበት ሁኔታ ሜዳውን ለዚህ መሰሪና አጥፊ ቡድን ለብቻ መተው አይገባም ከሚል ፣ ሁለተኛ በዲያስፖራ ተበታትኖ ያለውንና ከቀሪው ኢትዮጵያው ወገኑ በመተባበር መደረግ ከሚገባው የጋራ ትግል ራሱን አግልሎ ያለውን የማይናቅ ቁጥሩ ያለው ትግርኛ ተናጋሪ ለማሰባሰብ ከሚልና በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በህወሓት ጠባብ ብሄርተኛ አመለካትና መጥፎ ድርጊቶች ምክንያት በህወሓትና በትግራይ ህዝብ መካከል ያለውን ግዙፍ ልዩነት በተገቢ ደረጃ ሳያገናዝቡ በትግራይ ህዝብ ላይ በተለያየ ጊዜ አሳሳች መልእክት ሲያስተላልፉ የነበሩትን አክራሪዎች ለመታገል በሚል ነበር።

ዓአትዴማ ሀገራችን አሁን ገብታበት ያለችውን የህልውና አደጋ በዚህ ባሳለፍነው 6 ወራት በሚገባ ገምግሟል። ከዚህ ሰፊ ግምገማ በኋላ አብዝሃ አባላቱ አሁን ወቅቱ የአደረጃጀት ለውጥ እንድናደርግ ያስገድደናል፣ ወቅቱ በህብረብሄር ደረጃ ተደራጅቶ ሁሉንም ያሳተፈ ትግል ለማድረግ መነሳት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ላይ ደርሰናል። ይህ ስንል ግን ዓአትዴማ ከምስረታው እስካሁን ሲያደርገው የቆ እንቅስቃሴና ትግል ትክክል አልነበረም ከሚል አይደለም የአደረጃጀት ለውጥ አሁን ያስፈልጋል የምንለው። ዓአትዴማ ይዞዋቸው

የተነሳው ዓላማዎቹ አሁንም ሊያሰሩ የሚችሉ ትክክለኛ ዓላማዎች ናቸው ብለን እናምናለን። አሁን ካለው ሀገራችን በከፍተኛ የህልውና አደጋ የመግባት ሁኔታ አንጻር በብሄር ደረጃ መደራጀትና መታገል ሁኔታውን ለሚመጥንና ወቅቱ ለሚጠይቀው ለሁሉም አቀፍ ትግል እንቅፋት ይሆናል ከሚል ብቻ ነው በሀገር ደረጃ ተደራጅተን እንታገል የምንለው።

ሌላ አሁን ሀገራችን ገብታበት ካለቸው አደጋ ለማዳን በህብረብሄር ደረጃ ተደራጅቶ መታገል ያስፈልጋል ስንል በብሄር ደረጃ የመደራጀት ዴሞክራሲያዊ መብትና በሀገራችን እስከሁን ድረስ ትክክለኛ መፍትሄ ያለገኘውን የብሄር ጥያቄ እንቃወማለን ማለት እንዳልሆነም ግልጽ እንዲሆን እንፈልጋለን። በኢትዮጵያ የብሄር ጥያቄ ነበር፣ ትክክለኛ መፍትሄ ገና አላገኘም፣ ይህ ጥያቄ ትክክለኛ መፍትሄ ማግኘት እንዳለበትም በጽኑ እናምናለን። የብሄር ጥያቄን በተመለከተ እምነታችን ይህ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ የኢትዮጵያ ህዝብ በማለት ፈንታ ልዩነትን ለማጉላትና ይበልጥ ለመከፋፈል የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች የሚባል የተንዛዛ አገላለፅ በዚህ ባሳለፍነው 18 ዓመታት በአገዛዙ ካድሬዎች በስፋት መቀስቀሱንና መለመዱን መዘንጋት የለብንም። አብዮታዊም ዴሞክራሲያዊም ያልሆነው የመለስ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የኢትዮጵያ ህዝብን ከፋፍሎ ለመግዛትና አንድነቱን አላልቶ እያንዳንዱ የቡድን ባለስልጣን የየራሱ ግዛት እንዲመስርት የሚያመቻችና ህዝብ በአንድነት ቆሞ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ በጥንካሬ እንዳይታገል የሚያደናቅፉ የተለያዩ አሻጥሮችን እየፈጸመ መሆኑንም በሚገባ ተገንዝበናል።

አገዛዙን እየተቃወምን አጋዛዙ የሚፈልገው መሰረታዊ ያልሆኑ ልዩነቶችን የሚያጎላ ብሄራዊ አደረጃጀት ብንከተል በተዘዋዋሪ የመለስ አደገኛና ከፋፋይ አቀጣጫን (dangerous and divisive trend) መከተልና ማጠናከር ይሆናል፣ በብሄር ስም መጠራቱ ለኢትዮጵያ አንድነት ማለትም ለስትራተጂያዊ ግባችን አያገለግልም የሚለው አብዝሃ የዓአትዴማ አባላት በሚገባ የተመለከትነውና የአደረጃጀታችን ለውጥ እንድናደርግ ያስደረገን ሌላኛው ምክንያት ነው።

ከብሄራዊ አደረጃጀት ወጥቶ በህበረብሄር ደረጃ መደራጀትና መታገል ያስፈልጋል ስንል የሁሉም ብሄረሰቦች መኖሪያ የሆነችው ሀገራችን አሁን ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ስለሆነች፣ እነዚህ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የዴሞክራሲ ጭላንጭል ፈጽሞ በጠፋበት፣ ለዚህ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማበብ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የሲቪክ ተቋማት በሌሉበት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በብሄር ጥያቄ ስም እየማለና እየተገዘተ ሁሉን ብሄሮች እያሰቃየና እያጠፋ ያለው አገዛዝ እስካላስወገድን ድረስ ምኑንም ተግባራዊ ለማድረግ ስለማይቻል ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የሁሉንም ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች የረገጠና የሀገራችን ህልውና አደጋ ውስጥ ያስገባ ሽብርተኛ በመለስ ዜናዊ የሚመራው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ መጀመሪያ መወገድ አለበት ከሚል ነው።

ወድ ኢትዮጵያዊያን ሆይ ሀገራችን እንደ ሀገር በመኖርና ባለመኖር መካከል በመስቀለኛ መንገድ ላይ ነች። ከዚህ አደጋ ሀገራችንን ለማዳን ኢትዮጵያውያን ያለን ምርጫ አንድና አንድ ብቻ ነው ። የኸውም ያሉንን ልዩነቶችና የርስበርስ ችግሮች ለጊዜው ወደ ጎን በማስቀመጥ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በአንድነት በመለስ ዜናዊ የሚመራውን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በማስወገድ ለሁላችን የሚበጅ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመስረት በጋራ መታገል ነው። በበኩላችን ወቅቱ የሚጠይቀው ይህ የጋራ ትግል ስለሆነ ለዚህ እንቅፋት ሊሆን የሚችል የነበረው በብሄር ደረጃ ተደራጅቶ መታገልን አባዛኛው የዓአትዴማ አባላት አቁመን ለዚህ ለጋራው ትግል ተዘጋጅተናል። ስለሆነም ይህ መግለጫ ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አብዝሃ የዓአትዴማ አባላት የነበርን በዓአትዴማ ስም አንቀጥልም፣ አደረጃጀታችንም እንደኛ የሚያስቡና ለሀገራቸው እንደኛ የሚጨነቁትን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ የሚጨምር በህብረብሄር ደረጃ እንዲሆን ወስነናል።

ጥሪ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ፣

ሀገራችን ከምንጊዜም በላይ በከፍተኛ የህልውና አደጋ ውስጥ ገብታለች። ሀገራችን አሁን ገብታበት ካለችው አደጋ ለማዳን የሚቻለው ሁሉም ልጆቿ እጅ ለእጅ ተያይዘን ሀገራችን እዚህ ሁኔታ ውስጥ ለከተተና ህዝባችን ለዚህ ላለፉት 18 ዓመታት በግፍ በሁሉም አከባቢ ለገደለ፣ ላሰረና ላሰደደ በመለስ ዜናዊ የሚመራው ሽብርተኛ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ለማስወገድና ከዚህ አገዛዝ በኋላ ህዝብ በነጻ ምርጫ

የራሱን መንግስት መመስረት እስከምችል ድረስ በጋራ ስንታገል ብቻ ነው ብለን አብዛኛው የዓአትዴማ አባላት የነበርን እናምናለን።
ስለዚህም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት የሚታምኑ፣ በብሄረሰቦች እኩልነት የምታምኑ፣ ባልተሸራረፈ ሙሉ ዴመክራሲያዊና ሰብኣዊ መብት የምታምኑ፣ አሁን በስልጣን ላይ ያለው በመለስ ዜናዊ የሚመራው የህወሓት/ኢህአዴግ ሽብርተኛ አገዛዝ መወገድ የምትቀበሉ፣ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ሊያቀፍ በሚችል የሲቪክ እንቅስቃሴ በጋራ በመመስረት ለመታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ሀገራችንን ከገባችበት አዘቅት ለማውጣት የህብረት ትግል ብቸኛ መንደግ ነው!!!
ሀገራችን በልጆቿ ሁሉ የተባበረ ትግል ከመለስ ዜናዊ ሽብርተኛ አገዛዝ ነጻ ትወጣለች!!!
ኢትዮጵያና ህዝቧ ለዘላለም ይኖራሉ!!!

አብዝሃ የዓአትዴማ አባላት